# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter Published by the Corporate Communications Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-21 ጥር ወር 2007 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-21 January 2015 G.C Release


በጤና ሳይንስ ኮሌጅ አደረጃጀቶችን ተጠቅሞ አሣታፊ መማር ማስተማር ሂደትን ለማጠናከር

---------------------------------------- 4

ህብረተሰቡ የግልና የአካባቢውን ንጽህና ካጠበቁ ከ80% በላይ የሚሆኑ የተላላፊ ሽታዎችን መከላከል እንደሚያስችለው መገለፁ

----------------------------- 6

ስለምርጥ ዘር ብዜት ምርትና ምርታማነት ብሎም ጥራት የተለያዩ ስልጠናዎችን፣ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በዩኒቨርሲቲውና በሌሎች አጋር አካላት እንዲያገኙ በማድረግ በክልላችን ብሎም በሀገራችን ጥራቱን የጠበቀ ምርጥ ዘር በማምረትና የዘር ዋስትናን በማረጋገጥ በዘር ብዜት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው

---------------------- 8

የስነ-ፅሑፍ ስራዎች የሰውን ልጅ ከማዝናናት ባሻገር በርካታ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አላቸው

--------------------------------------------- 15

## በውስጥ ገፆቻችን


- በሜጋ ፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና እየተሰጠ ነው..................................... 3
- ኮሌጁ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮዎች ለማሳካት አልሞ እየሰራ ነው.................................................. 4
- የሥነ-ምግብ ግንዛቤ ያላቸው የግብርና ባለሙያዎችን ለመፍጠር የሚያግዝ ስልጠና ተሰጠ.................. 6
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በደንበኛ አያያዝ ስልጠና ሰጠ ...................... 7
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ልኡክ ቡድን ደማቅ ሽኝት ተደረገለት .................................. 8
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ የስድስት ወራት አፈፃፀም አጥጋቢ መሆኑ ተገለፀ ................ 10
- ዩኒቨርሲቲው በ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል የተሻለ ውጤት ለማምጣት ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ተገለፀ........................ 11





0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

# Vision

## እ.ኤ.አ. በ2030 ከዓለም ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

Debre Markos University aspires to be world class University in 2030.

# ተልዕኮ
# Mission

## ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

Producing competent and innovative professionals through providing quality instructional, CoCurricular and cultural involvement.

## አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders and,

## ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

Providing demand driven community and consultancy services.



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

# በሜጋ ፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና እየተሰጠ ነው

**ሙሀመድ ሰኢድ**

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮዎቹን በማሳካት ተመራጭ ዩኒቨርሲቲ የመሆን ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚያግዝ በሜጋ ፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና እየተሰጠ ነው፡፡



ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው የተሰጡትን ተልዕኮዎች በማሳካት ራዕዩን እውን ለማድረግ የመምህራንና ሰራተኞች አቅም በየጊዜው ሊገነባ ይገባል፡፡ ይህ ስልጠናም ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት የላቀ ስራ ለመስራት ይችል ዘንድ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት ይፈጥራል ብለዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ጥላዬ ገለፃ በሜጋ ፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ላይ የሚሰጠው ስልጠና ሁለተኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜን እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት መሰጠቱ ለዩኒቨርሲቲው የተሻለ እቅድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ በበኩላቸው የስልጠናው መሰጠት ዩኒቨርሲቲው በፕሮጀክት ቀረፃ ላይ የነበረበትን የአቅም ችግር በመቅረፍ በርካታ ለጋሽ ድርጅቶችን ለማፍራት ያስችለዋል ብለዋል፡፡

የሜጋ ፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ስልጠናው የረጅም ጊዜ የትምህርት፣ የምርምርና የፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር ልምድ ባላቸው ዶ/ር ጌትነት ገበየሁ እና ዶ/ር ሀፍቱ አሰፋ የሚሰጥ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በስልጠናው ላይ ከዩኒቨርሲቲው ሁሉም ኮሌጆች የተውጣጡ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

መምህራን እየተሳተፉ ሲሆን ስልጠናው እስከ ጥር 28/2007 ይቀጥላል፡፡ በስልጠናው ላይ የፕሮጀክት ዝግጅት ምንነት፣ አዘገጃጀት፣ በዝግጅት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮች እንዲሁም የተግባር ልምምድ ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡




ዶ/ር ጌትነት ገበየሁ የመጽሐፍት ስጦታ ሲያበረክቱ

በተያያዘ ዜና በስልጠናው መክፈቻ ላይ ዶ/ር ጌትነት ገበየሁ የተማሩባቸውን መፃህፍት የምርምር ጽሁፍችና መጠቀሚያ መፃህፍት ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በስጦታ ማበርከታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዶ/ር ጌትነት በምርምር ስራዎቻቸው ዘጠኝ የስንዴ ዝርያዎችን ማበርከታቸው ይታወቃል፡፡

## ኮሌጁ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮዎች ለማሳካት አልሞ እየሰራ ነው

**ሙሀመድ ሰኢድ**

ቴክኖሎጅ ኮሌጅ ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮዎች ስኬት አልሞ እየሰራ መሆኑ ተገለፀ፡፡

የቴክኖሎጅ ኮሌጅ ዲን አቶ ግርማው ተሻገር እንደገለፁት ኮሌጁ በ2007 ዓ.ም. አጠቃላይ እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በዚህም በበጀት ዓመቱ የመማር ማስተማር ስራውን ስኬታማ ለማድረግ በ172 መምህራን ከ5259 በላይ መደበኛ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ የሚገኝ ሲሆን አጠቃላይ የተማሪ ማቋረጥ መጠንም ወደ 2 በመቶ ለመቀነስ አቅዷል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication



አቶ ግርማው የ2007 ዓ.ም አፈጻጸምን ሲገልጹ

እንደ አቶ ግርማው ገለፃ በ2007 ዓ.ም. ኮሌጁ የተሻለ የስራ እንቅስቃሴ የነበረው ሲሆን የመምህራን የስራ ተነሳሽነት መጨመር፣ የጊዜ አጠቃቀም መሻሻል እና ኮርስ መሸፈን መቻሉ አበይት ስኬቶች ነበሩ፡፡ በበጀት ዓመቱ የፈተና ስርአቱም በተሻለ ደረጃ እንዲጠናከር ተደርጓል፡፡

ኮሌጁ በ2007 ዓ.ም. 14 ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀትና በማስተቸት ወደ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ለመላክ በቅቷል፡፡ በዚህም የቀረቡ ፕሮፖዛሎች የማህበረሰቡን ችግር መፍታትና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮፖዛሎች ወደ ፕሮጀክት ደረጃ እንዲያድጉ በተጠየቀው መሠረት ወደ ፕሮጀክት ለመቀየር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ቀሪዎቹ ፕሮፖዛሎችም በምርምርነት ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡ እንደ ኮሌጁ ዲን ገለፃ ቴክኖሎጅ ኮሌጅ የማህበረሰብ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ ለደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አገልግሎት መረጃዎች አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አተናተን የሶፍት ዌር ስልጠና ከመሰጠት ባሻገር የመንገድ ዲዛይን ስራውንም አጠናቆ አስረክቧል፡፡ በአሁኑ ሰአትም የከተማውን የመሬት አስተዳደር በዳታ ቤዝ ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ስራው ሲጠናቀቅ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከብክነት ማስቀረት ያስችላል፡፡ ኮሌጁ ከመንቆረር አግሮ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ ጋር በመተባበር የአማራ ገጠር መንገድ ስራዎችን የማማከር ስራ በመስራትም ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ ማስገኘት ችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ከደብረ ማርቆስ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በተፈረመው የጋራ መግባቢያ ሰነድ መሰረትም በርካታ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

በቀጣይም በምስራቅ ጐጃም ዞን አንዳንድ ቀበሌዎች በባህላዊ መንገድ ይወጣ የነበረውን የአረቄ አወጣጥ ወደ ዘመናዊነት ለመለወጥ እና የጤፍ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ቴክኖሎጅዎችን ለማመንጨት እቅድ ይዞ እየሰራ ነው፡፡

በመጨረሻም ኮሌጁ ተልኮዎችን ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የግዥ ስርዓት መጓተት፣ የግብአት በተለይም የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመሟላት እና መሰል ችግሮች ትኩረት ተሰጥቶባቸው ሊሰሩ ይገባል ብለዋል፡፡

## የሥነ-ምግብ ግንዛቤ ያላቸው የግብርና ባለሙያዎችን ለመፍጠር የሚያግዝ ስልጠና ተሰጠ

ሙሀመድ ሰኢድ

የሥነ-ምግብ ግንዛቤ ያላቸው የግብርና ባለሙያዎችን ለመፍጠር የሚያግዝ ስልጠና ተሰጠ፡፡ ስልጠናው ጀሂፔጎ (Jhpiego) በተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሴቭ-ዘችልድረን እና የአሜሪካ በጐ አድራጐት ድርጅት ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡



የሥልጠናው ክፊል ገጽታ

በጀሂፔጎ የስነ-ምግብ ቅድመ ትምህርት አማካሪ እና የስልጠናው አስተባባሪ አቶ መብት ከበደ እንደገለፁት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አርሶ አደሮች በስነ-ምግብ ላይ ያላቸው ግንዛቤና ልምድ ዝቅተኛ ነው፡፡ የስልጠናው ዋና ዓላማም መምህራንን በማሰልጠን



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

በተማሪዎቻቸው አማካኝነት የአካባቢውን አርሶ አደሮች ግንዛቤ ማሳደግ ነው፡፡ በመሆኑም ስልጠናው የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ መምህራን የግብርናውን ምርታማነት ከማሳደግ ባሻገር ተማሪዎቻቸው በስነ-ምግብ ላይ ቂልፍ ግንዛቤ እንዲጨብጡ በማድረግ የተሻለ ግንዛቤ ያለው አርሶ አደር ለመፍጠር ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መብት ገለፃ ለዩኒቨርሲቲው መምህራን በተዘጋጀው ስልጠና ላይ ከግብርናና ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ኮሌጅ የተውጣጡ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ እጽዋት ሳይንስ፣ እንስሳት ሳይንስና ገጠር ልማት ትምህርት ክፍል መምህራን ተሳትፈዋል፡፡ በስነ-ምግብ ጽንሰ ሃሳብ ላይም ሰፊ ውይይት አድርገዋል፡፡

በስልጠናው ላይ ያገኘነው የአግሮ ኢኮኖሚክስ ትምህርት መምህር አቶ ይበልጣል በላቸው እንደገለፁትም በስልጠናው ላይ ስነምግብን አስመልክቶ ያሉ ችግሮችን በሚመለከት በርካታ የጥናት ውጤቶችን እና ችግሩን ለመቅረፍ መወሰድ የሚገባቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች እንድናውቅ አድርጎናል ብለዋል፡፡ በአጠቃላይም የስልጠናው መዘጋጀት መምህራንና ተማሪዎች በስነምግብ ላይ ግንዛቤ ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል እውቀት እንደፈጠረላቸው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ስልጠናው ከጥር 25-29/2007 ዓ.ም. እንደተሰጠ እና ድርጅቱም በሀዋሳ፣ ጅማ፣ ጐንደር፣ መቀሌና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የተለያዩ የግብርናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች እንደሚሰራ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በደንበኛ አያያዝ ስልጠና ሰጠ

**ሰለሞን አበበ**

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ከደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በደብረ ማርቆስ ከተማ ለሚገኙ የሆቴልና ሬስቶራንት ባለቤቶች፣ አሥተናጋጆች እና የሆቴል ስራ አስኪያጆች በአገልግሎት አሰጣጥ እና በደንበኞች አያያዝ ላይ ያተኮረ የአንድ ቀን ስልጠና በጐዛምን ሆቴል ሰጠ፡፡





## የስልጠናው ክፊል ገጽታ

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ እንደተናገሩት የቱሪዝምና የሆቴል ኢንዱስትሪ እንዲሁ የሚገባበት ዘርፍ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባዮች ናቸው የሚባለው በሆቴሎቻችን አገልግሎት አሰጣጥ እየታየ ባለመሆኑ በሆቴል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ይህ ስልጠና ልዩ ጥቅም እንዲኖረው ገልፀዋል፡፡ ይህ ስልጠና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችን የእውቀት እና የክህሎት ክፍተቶች በመሙላት በአገልግሎት አሰጣጥ እና በደንበኞች አያያዝ ዙሪያ ውጤታማ ስራዎችን በመስራት የከተማችንን ገጽታ በመገንባት የኮንፈረንስ ማዕከል እድትሆን ያስችለናል፡፡ የደንበኞች አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ መጓደል ከተማችንን በሚጠበቀው መጠን እንዳታድግ አድርጓታል፡፡ ስለሆነም በሆቴላችን ለአንድ ቀንም ቢሆን የተስተናገደ ደንበኛ ቱሪስታችን እንደሆነ በማወቅ አገልግሎት አሰጣጣችንን እና የደንበኛ አያያዛችንን ትኩረት ሰጥተን ወላጆቻችን ያሳዩንን የእንግዳ አቀባበል ባህል ማስቀጠል አለብን በማለት ገልፀዋል፡፡

በስልጠናው "የአገልግሎት አሰጣጥና ደንበኞች አያያዝ " የሚል የስልጠና ሰነድ በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የማኔጅመንት ትምህርት ክፍል መምህር በሆኑት አቶ ኤርሚያስ ሀይሉ ቀርቧል፡፡ አቶ ኤርሚያስ በስልጠናዉ ስለ አገልግሎት ምንነት፣ ስለ ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የደንበኞች አያያዝ ጽንሰ ሃሳብ ሠፊ ገለፃ አድርገዋል፡፡

"የአገልግሎት አሰጣጥ መጓደል በጤና ላይ የሚያስከትለው ችግር" የሚል የስልጠና ሰነድ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር በሆኑት አቶ ቸሩ ተሰማ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ አቶ ቸሩ ምግብ የሚበከልባቸውን መንገዶች፣ ስለ ምግብ ወለድ በሽታዎች፣ የምግብ ወለድ በሽታዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻልና የምግብ ብክለት መከላከያ መንገዶች ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡

"የቋንቋ አጠቃቀምና የደንበኛ አያያዝ የሚል" ስልጠና የሰጡት ከሶሻል ሳይንስና ሰብአዊነት ኮሌጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህር አቶ ሀይማኖት ጌታቸው ናቸው፡፡ መምህር ሃይማኖት በድምጽ እና በድምጽ አልባ ግንኙነቶች ዙሪያ፣ ክብር ሊያሳዩ በሚችሉ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ከደንበኞች ትዕዛዝ ስንቀበል ምን ማድረግ እንዳለብን እና እንደሌለብን፣ የምንታዘዘውን ነገር በትኩረት እንዴት ማዳመጥ እንደሚገባን፣ የሰውነት አቋቋማችን ደንበኛውን እያዳመጥን መሆኑን ለማሳየት እንዴት መሆን እንዳለበት እንዲሁም ከስልክ ደንበኞችን ስናናግር የድርጅቱን ስም በትህትና በማስተዋወቅ በተረጋጋ መልኩ በግል መረጃ መሰጠት እንደሚባ ሰፊ ገለፃ አድርገዋል፡፡

በስልጠናው "የደንበኞች አያያዝና የአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስከትለው ስነ ልቦናዊ ጉዳት" የሚል የስልጠና ሰነድ በሶሻል ሳይንስና ሰብአዊነት ኮሌጅ የስነልቦና ትምህርት ክፍል መምህርት



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

ሀረገወይን ጥሩዬ ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም "የደንበኛ አያያዝና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው" የሚል የስልጠና ሰነድ ከደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር በመጡ የምጣኔ ሃብትባለሙያ አቶ ባንታየሁ ታምሬ ለሰልጣኞች ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም የጐዛምን ሆቴል ጀነራል ማናጀር አቶ ተካ ይመር ስለሆቴሉ የአሰራር ሁኔታ ለስልጠና ተሳታፊዎች ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡ እንደ አቶ ተካ ማብራሪያ የሆቴል ኢንዱስትሪ አስቸጋሪ የስራ ዘርፍ ነው፡፡ ስለሆነም ስራው በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መሠራት አለበት፡፡ በሀገራችን ያለውን የሆቴል ማኔጅመንት ችግር የጠቀሱት አቶ ተካ የጐዛምን ሆቴል ሰራተኞችን ለመቅጠር ማስታወቂያ እንደሚያወጣና በወጣው ማስታወቂያ መሰረት የተመዘገቡ ባለሙያዎችንም በመምረጥ በሙከራ ቅጥር ለ45 ቀናት ወደ ስራ እንደሚያሰማራ አስረድተዋል፡፡ በጐዛምን ሆቴል አንድ ሰራተኛ ከተቀጠረ በኋላ ስልጠና እንደሚሰጠውና ስለሚሰራው ስራ የስራ መዘርዝር ተሰጥቶት ወደ ስራ እንደሚገባም ጀነራል ማናጀሩ ገልፀዋል፡፡ የስልጠናው ተሳታፊዎችም በቀረቡት የስልጠና ሰነዶች ዙሪያ ሠፊ አስተያየት እና ጥያቄዎችን አንስተው ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ልኡክ ቡድን ደማቅ ሽኝት ተደረገለት

**ሰለሞን አበበ**

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል በአዳማ ዩኒቨርሲቲ የሚሳተፈው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስፖርት ልኡክ ቡድን በፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖችና ዳይሬክቶሬት በደማቅ ሁኔታ ሽኝት ተደረገለት፡፡





*ዶ/ር ጥላዬ ጌታ ለልኡክ ቡድኑ የሥራ መመሪያ ሲሰጡ*

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት፣ ዶ/ር ጥላዬ ጌታ የስፖርት ልኡክ ቡድኑ ሽኝት ፕሮግራም ባደረጉት የሥራ መመሪያና የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግራቸው እንደገለፁት የስፖርት ልኡክ ቡድኑ ተቀዳሚ ዓላማ መሆን የሚገባው ስፖርታዊ ጨዋነትን ተላብሰው የዩኒቨርሲቲውን አካባቢ ባህል ለሌሎች ማስተዋወቅና እነሡም የሌሎችን በማወቅ የእርስ በእርስ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

የልምድ ልውውጥ በመፍጠር የተለመደውን ሥነ ምግባር ማጕልበት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ በ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ተካፋይ የሚሆኑት የተለያዩ የስፖርት አይነት ተሳታፊ ተማሪዎችን በቅድሚያ እንኳን የ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት ትምህርታችሁ ፍፃሜ አደረሳችሁ ያሉት ዶክተሩ ሁሉም የልኡክ ቡድኑ አባላት ቡድን መሪ በመሆን ስነ-ስርዓትን በማክበርና በማስከበር በሁሉም የልኡክ ቡድኑ እንቅስቃሴ የዩኒቨርሲቲውን አካባቢ ባህል ከሀዲስ አለማየሁ ባህል ቡድን ጋር በመሆን መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ ለዚህም ሁሉም የልኡክ ቡድን የቀን ከቀን ውሎውን አደረጃጀቶችን በመፍጠር ግምገማ ማድረግ እና ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ መፍታት እንደሚገባ አስምረው ተናግረዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም የስፖርት ተወዳዳሪዎች በሚሳተፉባቸው የስፖርት ውድድሮች ተገቢ የሆነ ስነ ምግባር በመላበስ መጫዎትና ደጋፊዎችም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የዩኒቨርሲቲው አምባሳደሮች በመሆን ያለውን መልካም ዝና የበለጠ አጕልብተውና ውጤት አስመዝግበው መምጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ ዶ/ር ጥላዬ ጌታ በመጨረሻም የስፖርት ልኡክ ቡድኑ የዩኒቨርሲቲውን ገጽታ ለመገንባት የስፖርት ፌስቲቫሉ ተሳታፊ ልኡክ ቡድን ሁሉም በጋራ የአካባቢውን ቱባ ባህል የማስተዋወቅና እሡም የሌሎችን የማወቅ ጥረት ማድረግ እንደሚገባው ተናግረዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን ስፖርታዊ ውድድሮችም በተለያዩ ዘርፎች ከስፖርት ፌስቲቫሉ መልስ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም እምነታቸውን ገልፀዋል፤ ለስፖርት ልኡክ ቡድኑም መልካም ምኞት ተመኝተዋል፡፡

በስፖርት ልኡክ ቡድኑ የሽኝት ፕሮግራም ላይ የተማሪዎች አገልግሎት ቡድን መሪና በኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሽዋዬ ብርሃኑ በበኩላቸው ለ2007 ዓ.ም. የስፖርት ፌስቲቫል ዝግጅት የተለያዩ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውኑ መቆየታቸውን ገልፀው ዩኒቨርሲቲው ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የስፖርት ተሳታፊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ጥናት ተቋም ከስፖርታዊ ውድድሮች ባሻገር የዩኒቨርሲቲውን አካባቢ ማህበረሰብ ባህል ለማስተዋወቅ እስካሁን ያደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በፊት በተሳተፉባቸው የተለያዩ የስፖርት አይነቶችም ሜዳሊያዎችን ማምጣት መቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በ2007 ዓ.ም. ተሳታፊ የስፖርት ልኡክ ቡድንም የተለያዩ ስልጠናዎችንና ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ገልፀው አመራሩ፣ የደብረ ማርቆስ ከተማ ስፖርት ጽ/ቤት የዩኒቨርሲቲው የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል፣ ፖሊስ፣ ክሊኒክና እንዲሁም ሌሎች አካላት ሲያደርጉት ለቆዩት ድጋፍና እርዳታ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲው በሚሳተፍባቸው ስፖርታዊ ውድድሮች የተሻለ ውጤት አስመዝግቦ እንደሚመለስ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

አጠቃላይ የልኡክ ቡድኑ ብዛትም ወንድ 119 እና ሴት 47 በድምሩ 166 መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም በሽኝት ፕሮግራም ላይ የዩኒቨርሲቲውን አካባቢ ባህል ከአዳማ ለማስተዋወቅ ከሚያቀርባቸው ዝግጅቶች መካከል እንደ ቅኔ ዘረፋ፣ መነባንብ እንዲሁም ቅረርቶዎች ለፕሮግራሙ ታዳሚዎች በማቅረብ አድናቆትን አግኝተዋል፡፡

ተሳታፊዎችም የተለያዩ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ ለቀረቡት ጥያቄዎችም ምላሾች የሚመለከታቸው አካላት ሰጥተውባቸዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የስፖርት ልኡክ ቡድን

በየተመደበበት መኪና እንዲጓዝና አዳማ ሲደርስም በዩኒቨርሲቲው ቁልቢ በር እንደሚገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ የስድስት ወራት አፈፃፀም አጥጋቢ መሆኑ ተገለፀ

**ሰለሞን አበበ**

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጡ የለውጥ መሣሪያዎች በመተግበሩ እና የልማት ሰራዊት ግንባታውን በማጠናከሩ በ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያው ግማሽ አመት አፈፃፀም አጥጋቢ መሆኑ ተገለፀ፡፡




አቶ ጠግቤው ዋለ የቡሬ ካምፓስ ዲን ገለፃ ሲያደርጉ

የካምፓሱ ዲን አቶ ጠግቤው ዋለ እንደገለፁት ከካምፓሱ አዲስነት ጋር ተያይዞ የካምፓሱን መዋቅር በ2006 ዓ.ም. ጀምሮ ኮሚቴ በማቋቋም ተጠንቶ ፕሮፖዛል ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በመዋቅሩ ምን ሰራተኛ ሊካተት ይገባል የሚለውን ደግሞ የስራ መደቦች በዝርዝር በማጥናት እና ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ቀርቦ በማስገምገም በሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት በኩል ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ መደቦች ፀድቀዋል፡፡ በፀደቀው መደብም የሰው ሃይል ለማሟላት ማስታወቂያ በማውጣት በደረጃ እድገት፣ በዝውውርና በቅጥር የዩኒቨርሲቲው ሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት ሰራተኞችን የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡

በዚህም ሰፊውን ጊዜ በመጠቀም መዋቅሩን የመስራት እና የሰው ሃይሉን የማሟላት ስራ በመሠራቱ እና ከዋናው ግቢ ጋር ትስስር በመፍጠሩ የካምፓሱ አፈፃፀም በአጥጋቢ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡ ምንም እንኳን ካምፓሱ አዲስ ቢሆንም ያሉት ሰራተኞች ጥሩ የቡድን ስሜት

በመፍጠራቸው የተሻሉ ስራዎች በዝግጅት ምዕራፍ ነሀሴ ወር ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥም የተማሪዎች መፀዳጃ ቤቶች ግንባታ የእጅ መታጠቢያ፣ የልብስ ማጠቢያ እና የሻወር ቤት ተሰርቷል፡፡



በዝግጅት ምዕራፍ የተሰሩ የእጅ መታጠቢያና የሻወር ቤቶች

እንደ አቶ ጠግቤው ዋለ የቡሬ ካምፓስ ዲን ማብራሪያ የተሰራውን መዋቅር ተጠቅሞ የዩኒቨርሲቲውን ሦስት ተልኮዎች እያከናወነ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን እንደአጠቃላይ የካምፓሱ አፈፃፀም አጥጋቢ ቢሆንም በመማር ማስተማር ካምፓሱ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በካምፓሱ የተደራጀው የትምህርት ልማት ሰራዊት በተሻለ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ በልማት ቡድንና በአንድ ለአምስት እቅዶች እየታቀዱ እና አፈፃፀማቸውም በተማሪዎች፣ በመምህራን እና በሰራተኞች ውይይት እየተደረገበት ይገኛል፡፡

ሴቶችን እና በአካዳሚክ ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎችን ለመደገፍ በየኮርሱ መምህራን የቱቶሪያል ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎችን የተግባር ትምህርት ለመስጠትም መኪና ትብብር በመጠየቅ የሹፌር አበል እና የነዳጅ ወጭ በመሸፈን ብርሸለቆ፣ አየሁ፣ ቁጭ የሚባሉ ቦታዎች ተማሪዎችን በመውሰድ በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን በተግባር እንዲያዩ ጥረት ተደርጓል በማለት አቶ ጠግቤው ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ጠግቤው ገለፃ በማህበረሰብ አገልግሎት ዙሪያ ለአካባቢው የንግድ ማህበረሰብ በግብር ጽንሰ ሀሳብ እና አስፈላጊነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአራት ትምህርት ክፍሎች በሆርቲካልቸር፣ በእጽዋት ሳይንስ፣ በደን ሳይንስና በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ትምህርት ክፍሎች ለምርምር፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት እና ለማስተማር እንዲሁም ለገቢ ማመንጫ የሚሆን ፕሮጀክት ተነድፎ ደረጃውን የጠበቀ ነርሰሪ ሳይት በመመስረት ወደ ስራ ለመግባት በሒደት ላይ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ጠግቤው እንደገለፁት የተማሪዎች የምግብ አቅርቦት እንዳይስተጓጎል ግብአቶች ከዩኒቨርሲቲው እየቀረበ ይገኛል፡፡ የዳቦ አቅርቦት ጉዳይ አውትሶርስ ተደርጎ በተለያዩ ምክንያቶች እንቅፋት ሲሆን ቆይቷል፡፡ ነገር ግን አሁን በካምፓሱ የዳቦ አቅርቦት ጉዳይን ለመፍታት ከዩኒቨርሲቲው የዳቦ መጋገሪያ ማሽን በማስመጣት ስራዎች እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የመብራት መቆራረጥ ችግር ስላለ ይህን ችግር ለመቅረፍ የጀነሬተር ግዥ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication

ለመፈፀም በሒደት ላይ ነው፡፡ በዚህም የዳቦ አቅርቦት ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ይፈታል በማለት አቶ ጠግቤው ጨምረው ገልፀዋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው በ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል የተሻለ ውጤት ለማምጣት ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ተገለፀ

ሁሉንአየን ጋሻው

ደ/ማ/ዩ፡- ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ከጥር 23- የካቲት 8 2007 ዓ.ም. በሚካሄደው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል በሚሳተፍባቸው ሁሉም የስፖርት አይነቶች ውጤታማ ለመሆን ዝግጅት ማድረጉን ገለፀ፡፡




በስፖርት ልምምድ ላይ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የስፖርትና መዝናኛ ባለሙያ እና የአለም አቀፍ ቴኳንዶ አሰልጣኝ አቶ ሳምሶን ግዛቸው እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው ለ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል በሚካፈልባቸው የስፖርት አይነቶች በዩኒቨርሲቲው የስፖርት ሳይንስ መምህራን በሳምንት ለ5 ቀናት ስልጠና እየተሰጠ ነው፡፡ አያይዘውም ተማሪዎች በተለያዩ ስፖርት አይነቶች መሳተፋቸው በአካልና በአዕምሮ ጐልብተው የተግባቦት ክህሎታቸው የተሻለ እንዲሆን ያስችላል ብለዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አለም አቀፋዊ አስተሳሰብ በመያዝ የዳበረ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች በንቁ ዓዕምሮ ትምህርታቸውን ለመከታተልና ውጤት በማስመዝገብ የተሻለ ህይወት ለመምራት ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡ በመሆኑም ለራሳቸውም ሆነ ለሀገራቸው ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያስችላቸው አክለው ገልፀዋል፡፡

በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለሚሳተፉ ስፖርተኞችና አሰልጣኞች ዩኒቨርሲቲው የስልጠና ግብዓቶችንና የተለያዩ ድጋፎችን እየሰጠ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ለዚህም የዩኒቨርሲቲው አመራር ለስፖርቱ እያደገ ያለው ድጋፍ አበረታች መሆኑን እና ስፖርተኞችም ከሚያደርጉት የልምምድ እንቅስቃሴና ብቃት አንፃር የተሻለ ውጤት ለማምጣት እየሰሩ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አገልግሎት ቡድን መሪ እና የሀገሪቱ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሸዋየ ብርሀኑ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው

በስፖርት ፌስቲቫሎች መሳተፉ ከሌሎች ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ የአካባቢውን ባህል ለሌሎች ለማስተዋወቅ፣ የሌሎችንም ለማወቅ ያስችላል ብለዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለፃ ፕሮግራሙ የስፖርት ፌስቲቫል ብቻ ሳይሆን ወጣቶች አንድነትን፣ ፍቅርንና ሀገራዊ ራዕይን እንዲሰንቁ ያስችላል፡፡ በሌላ በኩል ስፖርታዊ ወድድሮች በዩኒቨርሲቲዎች መካሄዳቸው ተቋማቱ የውድድር ሜዳዎችን ማዘጋጀት ሰለሚገባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ ጤንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ለማፍራት ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡ በማጠቃለያ ንግግራቸው የዩኒቨርሲቲያችን ስፖርተኞች የተለመደውን ስፖርታዊ ጨዋነት አዳብረው በአለፈው ዓመት ያገኙትን ደረጃ ይዘው እንደሚመለሱ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለዚህም እያንዳንዱ ተጫዋች ተግባርና ኃላፊነቱን ተረድቶውልመያዙ ተጠቁሟል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል በእግር ኳስ በመረብ ኳስ፣ በጠረጴዛ ቴንስ፣ በቼዝ፣ በሩጫ፣ በፖራ ኦሎምፒክስ ወንድና ሴቶች በአለም አቀፍ ቴክዋንዶ በወንዶች እና በሴቶች እንዲሁም በቅርጫት ኳስ በወንዶች ብቻ እንደሚሳተፍ ተገልጿል፡፡

በመጨረሻም አቶ ሳምሶን ግዛቸው በመልካም ምኞት መግለጫ ንግግራቸው ስፖርት አለምን አንድ የማድረግ ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ከዚህ በፊት የጀመረውን የውስጥ ለውስጥ ውድድሮች በማጠናከር በስፖርት ቀዳሚነቱን ማረጋገጥ ይገባዋል ብለዋል፡፡ ለዚህም የበላይ አመራሩ ለስፖርት ያለውን ቆራጥ አመራርና ድጋፍ አጠናክሮ የሚቀጥል ከሆነ ዩኒቨርሲቲው በስፖርቱ ዘርፍ ውጤታማ እንደሚሆን እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል በየዓመቱ የሚካሄድ ደማቅ ፌስቲቫል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ዩኒቨርሲቲዎች የእርስ በርስ ትስስራቸውን በማጠናከር ተማሪዎች የልምድ ልውውጥ ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረላቸው መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ የ2006 ዓ.ም. ስፖርት ፌስቲቫል በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት መካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡ በ8ኛው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል ተሳታፊ የሚሆነው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስፖርት ልኡካን ወንድ 118 ሴት 47 በድምሩ 165 መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**0913-14-96-80** **Fax. 058-771-17-64** ✉ **269** E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook:dmu comunication